



# የመጽሐፍ - ቅኝት

የመጽሐፍ ርዕሥ--------ዴርቶጋዳ
ደራሲ ------------ይስማዕከ ወርቁ
አስተያየት --- መስፍን ማሞ ተሰማ




**እንደ መነሻ !**

አንባቢያን ሆይ! ዴርቶጋዳን በማንበቤ ሠላም አጥቼ ሰነበትኩ።ነፍሴ በከፍተኛ ማዕበል ስትናወጥ ከረመች።ቃላት ሊገልጹት የማይችል ጥልቅ ሃዘን ፤ ደግሞም ተስፋ ፤ ደግሞም ብሩህ ራዕይ፤ ተፈራረቀብኝ።

ማዕበሉ ጸጥ ሲል ነፍሴም መልህቋን ስትጥል፦ ለብዙ ማዕልትና ሌሊት በጥሞና አሰላልሰልኩ።ከነፍሴ ጋር ተማከርኩ ።

እርግጥ ነው! የዴርቶጋዳ መለኮታዊ ምሥጢራት ሁሉ ገና አልተገለጡልኝም። ምናልባትም አይገለጡልኝም ይሆናል።ነፍሴ ግን መተንፈስ ፈለገች። ከጭንቀቷ መገላገል!። ስለ ዴርቶጋዳ መናገር…።

እና ብዕሬን አነሳሁ። እንሆ ዴርቶጋዳን ከናንተጋ መጋራት ፈለኩ። ስለምን ደካማዋ ነፍሴ ታፍና ትሙት?!እናንተም ይህን ጽሁፍ አስጀምሮ ያስጨርሳችሁ ዘንድ ትዕግስታችሁ ይሁን!

**እንሆ ዴርቶጋዳ፦**

**<u>እኛም አለን ዳን-ብራውን!</u>**

ዳን ብራውንን የማያውቅ ወይም ስሙን ያልሰማ ይኖር ይሆን? የ"**ዳቪንቺ-ኮድ**" ደራሲ ነው። ብራውን በቅርቡ ያሳተመው "ዘሎስት ሲምቦል" መጽሃፉን ጨምሮ አምስት መጽሃፍትን ለንባብ አቅርቧል።

አንባቢ የብራውንን ድርሰቶች አንብቦ ሲጨርስ ነፍሱ እፎይታን አታገኝም።ሠላም አይኖራትም ፤ ዕውቀት ትጠማለች፤ ምስጢራት ሁሉ ይገለጡላት ዘንድ ጥንተ-ንታዊ ጥራዞችን ማገላበጥ ትሻለች። ይህ የብራውን ልዩ ችሎታ ነው።እነኘህ የዳን ብራውን ድርሰቶች ቀልቤን ማርከውት ከርመዋል።ከእንግዲህ ግን ጤና ሰንብት! ዳን ብራውን ነጻነቴን አውጃለሁ! ለማለት ተዘጋጅቻለሁ።

ፀሃይ በጠዋት ማልዳ አዲስ ቀን መውጣቱን ለአዲስ ዘር ለማብሰር፤ አድማስ ታካ ከወደ ምስራቅ አምራና ደምቃ ፍንትው እንደምትል ሁሉ፦…እንሆ ከወደ ምሥራቅ በዓለም የስነ-ጽሁፍ ማማ ላይ የወጣ "ዴርቶጋዳ" ርችት ተኩሷል። ተኳሹ ብላቴናም ይስማዕከ ወርቁ ይባላል።

እንሆ! በፓሪስ ኤፍል ታወር አናት ላይ ቆሜ፤ በኒው ዮርክ ስታቹ ኦፍ ሊበርቲ ሥገነት ላይ ወጥቼ ፤ በሲድኒ ሃርበርድ ላይ ተንጎራድጄ ፤ ዴርቶጋዳን አውጃለሁ። እኛም አለን ዳን ብራውን ብያለሁ!፡፡

**ማሔር ሻላል ሐሽ ባዝ**

በታላቁ መጽሃፍ ኢትዮጵያ ስሟ ተደጋግሞ ተነስቷል፡፡ ከሁሉም በላይ ግን ኢትዮጵያውያንን ጨምሮ አያሌ የአለም ተመራማሪዎችን ትኩረት የሳበው:- **"ኢትዮጵያ እጆቸዋን ወደ ፈጣሪ ትዘረጋለች"** የሚለው ነው። ኢትዮጵያ ዛሬም እጆቸዋን ወደ ፈጣሪ እንደዘረጋች ነው፡፡ **"እንኳኑ ይከፈትላችኋል፤ ዕሹ ታገኛላችሁም!"** ይላል የጌታ ቃል። ኢትዮጵያ በፀሎቷ የምትሻውን አላገኘችም። በሩም አልተከፈተላትም።

ለመሆኑ ስለምን ይሆን ኢትዮጵያ እጇቿን ወደ ፈጠሪ ዘርግታ የምትጸልየው? ጸሎቷስ ለነማን ነው? ፈጣሪዋስ የሚሰማት መቼ ነው? እንላለን እኛ፡፡ ለዚህ የዘወትር ጥያቄያችን ምላሽ የምናገኝበት ግዜ የመቃረቡን **"ትንቢት"** የቋጠረ ይሆን ዴርቶጋዳ:-?

የዴርቶጋዳ ደራሲ፡ ብላቴናው ይስማዕከ "ከላይኛው ደራሲ ዘንድ የተላከ ታላቅ መልዕክት በመንፈቀ ሌሊት በሬን በርግዶ ገብቶ ከእንቅልፌ አባነነኝ።ከወርቃማው ክንፉ ላይ አንድ ላባ ነቅሎ ብዕር ቀርጾ ሠጠኝ። በታላቅ ሰሌዳ ላይም:- ማሔር ሻላል ሐሽ ባዝ ብለህ ፃፍ አለኝ " ይለናል ድርሰቱን እያዋዛ ሲጀምር። ምን ማለት ነው? ይህ የስላሴዎች ቋንቋ ነው? ራዕይ የሚታያቸው ብቻ ሊገለጽላቸው የሚችል ቋንቋ? ደራሲውስ እንደ መልዕክተኛው ጳውሎስ ለኢትዮጵያችን የራዕይ መልዕክተኛ ይሆን? እንላለን።

በመለኮት ቋንቋ ማሔር ሻላል ሐሽ ባዝ ማለት:- ምርኮ ፈጠነ ብዝበዛ ቸኮለ ማለት ነው ይለናል:- ሚስጥሩን የፈታልን ይስማዕከ።ተማራኪው ማነው ተበዝባዦችስ? ብዝበዛውስ መፍጠኑ ስለምንድነው? እንላለን እኛ። ምስጢራዊው ቋንቋ ይበልጥ በአይምሯችን እየተወሳሰበ።

«ኦርያ ኢትዮጵያ ማሔር ሻላል ሐሽ ባዝ» ይለናል ደግሞ:- በውድቅት ሌሊት የተነገረውን መልዕክት ሲያስተላልፍልን። አሁንም ምን ማለቱ ነው እንላለን! እንጠይቃለን!። ኦርያ ኢትዮጵያ ማሔር ሻላል ሐሽ ባዝ ማለት:- « የኢትዮጵያ ተባዮች ከላይዋ ላይ ተነሱ.....ምርኮ ፈጥንዋል....ብዝበዛም ቸኩሏል» ማለት መሆኑን ተርጉሞልናል ደራሲው።ያንተ ያለህ! እንላለን። "አይን አላቸው አያዩም ጆሮ አላቸው አይሰሙም" የሚለው የጌታ ቃል በሚያስገመግም መለኮታዊ ድምጽ በህሊናችን እያስተጋባ።

ዕውነት ነው:-! እንላለን። ኢትዮጵያ በተባዮች ተወራለች። ኢትዮጵያ ምርኮኛ ናት። እጇቿዋን ወደ ፈጣሪ የዘረጋችውም መማረኳን ስታሳይ ነው። አቅም ማጣቷን። ከምርኮ ነጻ የሚያወጣት አለማግኘቷን ።እርግጥ ነው አይተናል። እውነት ነው ሰምተናል። ብዝበዛውም ፈጥኗል። ሆድ ዕቃዋን ቦትርፈው አንጀቷን የሚዘረግፉ በዝተዋል።እንደ መስቀል ቅርጫም እየተቀራመቷትም ነው።

ለዘመናት አይተን እንዳላየን፤ ሰምተንም እንዳልሰማን ኖረናል። ሃጥያታችን በዝቷል፡፡ ወንጀላችን በርክቷል። እንደ ጲላጦስ እጃችንን ታጥበን:- በኢትዮጵያ ምርኮ የለንበትም ፤ ብዝበዛውንም አናውቅም ለማለት አንችልም፡፡ የፍርድ ቀን ተቃርቧልና።

**ማሔር ሻላል ሐሽ ባዝ:-** "እግዚአብሔርም ታላቅ ሠሌዳ ወስደህ ምርኮ ፈጠነ ብለህ በሰው ፊደል ጻፍበት። የታመኑት ሰዎች ካህኑን ኦርዮንን የበረክዩን ልጅ ዘካሪያስን ምስክሮች አድርግልኝ አለኝ" ይላል የኢሣያስ መፅሃፍ።

ይህ እንግዲህ ኢትዮጵያዊ የናሳው ሳይንቲስት ሻጊዝ ዕጅጉ ለትንሣዔ ኢትዮጵያ **ለዴርቶጋዳ** ያዘጋጀው፤ ዶ/ር ሚራዥ በቀይ ድንጋይ ላይ ተቀርጾ የደረሰው መልዕክት መጻህፍ ቅዱሳዊ ትርጉም ነው።

“አዎ!” አለ ሚራዥ፡ ቀዩን ድንጋይ እንደያዘ። “ምርኮ ፈጥኗል ፤ ብዝበዛም ቸኩሏል። ሃገሪቱ በቅጥረኞችና በአድርባዮች እየተበዘበዘች ነው:: ህዝቦቿ የበይ ተመልካች ሆነዋል። ተስፋ በቆረጠ ትውልድ ተሞልታለች። ወጣቶቿ እንጀራ ፍለጋ በባዕድ ሃገራት ገረድ እየሆኑ ነው። ማምለጫ ያጡትም በጥቁር አልማዛቸው ላይ ተኝተው እየለመኑ ነው:፤ አዎ! ጥቂቶች እየበዘበዙ ነው። ኢትዮጵያ የተሰበረ መንፈስ ውጧታል ። ምርኮ ፈጥኗል! ብዝበዛም ቸኩሏል።” ያንተ ያለህ! እንላለን....ምን ይሻላል? ምን ይበጃል? አርባ ማዕልትና አርባ ሌሊት ብንጾም፤ ብንጸልይና ብንሰግድ ፈጣሪ ይታረቀን ይሆን?... እራሳችን እንጠይቃለን!የለም ይለናል ዴርቶጋዳ፡- ‘ ጾም ጸሎት ለነፍሳችሁ ነው...። ለሥጋችሁ! ’ እናስ ምን ይሻለናል? ብለን መልሰን እንጠይቃለን።

“አንድ ነገር ያስፈልጋል! ለለውጥ ራስን መስጠት!። አሁንም ኢትዮጵያ አንድ አብዮት ያስፈልጋታል! ሳይንቲፊክ ሪቮሊሽን። በሳይንስና በቴክኖሎጂ የታገዘ አብዮት! ለውጥን የሚጠላ ኢትዮጵያዊ የለም። ለውጡ ሆዳቸውን ከሚያጎልባቸው ጥቂቶች በቀር። ችግሩ ግን የለውጡ አካል መሆን የሚፈልግ የለም:: በሌሎች ሞትና ደም ለመጠርቃትና ኑሯቸውን ለማደላደል የሚመኙ ግን ብዙ ናቸው።” ይለናል ከዓለማችን ዝነኛ ሳይንቲስቶች አንዱ፡- ሻጊዝ እጅጉ! በዴርቶጋዳ ላይ::

ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል? ግራ በመጋባት አሁንም እንጠይቃለን። የጥያቄችሁን መልስ ከሎሬት ፀጋዬ ገብረ መድህን ሥራዎች አንዱ ከሆነው **“ሠቆቃው ጴጥሮስ”** ሚስጥራዊ ሥነ ግጥም ውስጥ ታገኙታላችሁ ይለናል፡ ዴርቶጋዳ። እኛም መልሱን ለማግኘት ወደ ተጠቆምንበት አቅጣጫ እናመራለን፡-በጉጉት፤ በተስፋና በትጋት።

**ሠቆቃው ጴጥሮስ**

በ1961 ዓም (እ.እኛ.አ) አባ ዲዲሞስ ራዕይ ለተጠናወተው ወጣቱ ገጣሚ ፀጋዬ ገ/መ በአቁማዳቸው ውስጥ ይዘውት ከነበረው ብራና አርባ ስምንት(48) ቃላትን አውጥተው፡- አንድ መቶ አምስት (105)ስንኞች ባሉት “ሠቆቃው ጴጥሮስ” ሥነ-ግጥም ውስጥ በትኖ እንዲዘራቸው ባለቅኔው አዘዙት። አርባ ስምንቱን የአባ ዲዲሞስ ምስጢራዊ ቃላት ጨምሮ “ሰቆቃው ጴጥሮስ” 497 ቃላት ይዟል።

አርባ ስምንት ቃላት በሚስጥራዊ ቁጥሮች የተሞላውንና በ “ቶ” ፊደል ቅርጽ የተሰራውን **“ዴርቶጋዳ”** መስቀል ይፈታሉ። ይለናል ይስማዕከ። ታምር አያልቅም በዴርቶጋዳ! እንላለን እኛ። ለመሆኑ አባ ዲዲሞስ ማናቸው? እንጠይቃለን::

**አባ ዲዲሞስ፡-** የአባ ፊንሐስና የአባ ዣንበሩ ጓደኛ የነበሩ...የማፍያው የአባ ዲዖላ አባት፤ በሳይንቲስቲ ሻጊዝ እና በዶ/ር ሚራዥ ጀርባዎች ላይ የሚገኙትን የመስቀል ንቅሳቶች የሣሉ ፤...አቡነ ጴጥሮስ ኃውልት ላይ ሽንታቸውን እያንፎለፎሉ አቡኑን ሲሣደቡ....ከጸጋዬ ጋር ግብ ግብ የገጠሙ ናቸው። አባ ዲዲሞስ።

ስለምንድነው አባ ዲዲሞስ አቡነ ጴጥሮስ ሃውልት ላይ ሽንታቸውን መሽናታቸው? አቡነ ጴጥሮስ ምክሬን አልሰማኝ ብሎ ነው የሞተው ይላሉ አባ ዳዲሞስ። “ክፉ ነገርን ማለፊያ ጥበብ አልነገርኩህም ነበርን?.....አንተ ድንጋይ!?...ክፉ ቀንን ከማለፍ በላይ ጥበብ የለም!....አዎ! ይህንንም ነግሬህ ነበር። ይህቺ ደም መላስ የለመደች ሃገር የምትለውጥ መስሎሃል?..ስንት ጀግኖች ሞቱላት! ...አልተለወጠችም። ጴጥሮስ አልነገርኩህም?...አንተ ብትኖር ኖሮ ይሄኔ አቡነ ዲዲሞስ እባል ነበር። የዚህች ሃገር እጣ ፈንታ በእጃችን ይወድቅ ነበር:: እንለውጣት ነበር።....ጵጵስና ሳትሰጠኝ ሞትክ...” እያሉ ነበር አባ ዲዲሞስ በአቡነ ጴጥሮስ ኃውልት ላይ ሽንታቸውን የሚያንፎለፉሉት።

አሁንም በጥያቄ ብዛት አይምሯችን ይወጠራል።አቡነ ጴጥሮስና አባ ዲዲሞስ ሚስጥር ነበራቸው ማለት ነው? ኢትዮጵያን የመለወጥ እቅድ ነበራቸውን? ከሆነስ አቡኑና አባው ኢትዮጵያን የመለወጥ ራዕያቸው ምን ነበር? ሃይማኖትና ፖለቲካ? የሚሉ ጥያቄዎችን ያዥጎደጉዳል። ጉድ ነው!... እንላለን በአግራሞት።

"ይኸው እኚህኛው ጳጳስ የዳጋ እስጢፋኖስ ገዳም አበምኔት እንኳ ያድርጉኝ ብላቸው ከልክለውኝ አባ ዝንበሩን ሾሙት። አንተ ብትኖር ግን ወንበዴዎች ጳጳስ ሆነው አይሾሙም ነበር። እኔና አንተ የምናውቀው የዚህች ሀገር ምስጢር በወንበዴዎች እጅ አይገባም ነበር፡፡ ....ለምን ሥልጣን ሳትሰጠኝ ሞትክ?..." እያሉ የጠይቃሉ፤ ኃውልቱን።እኛም በጭንቀት ተውጠን ፤ ድንግላዊት ማሪያም አማልጅን እንላለን፡፡ በአባ ዲዲሞስስ ንግግር፡፡ጵጵስናውንም ወንበዴዎች እንደያዙት አባ ዲዲሞስ ሲያስታውሱን፡- እግዚኦ እግዚአ! ለመሆኑ ይህ ሁሉ ሲሆን የት ነበርን እንላለን ? ራሳችንን!እንጠይቃለን።

ታዲያ አባ ዳዲሞስ አቡነ ጴጥሮስን መስደባቸውና ኃውልቱ ላይ መሽናታቸው ሆን ብለው ነበር። ወጣቱን ባለቅኔና ገጣሚ ጸጋዬ ገ/መን ፡ አበሳጭተው ለማጥመድ።

"ድንጋይ አይደለም" ይላቸዋል ወጣቱ ገጣሚ በደም ፍላት፤ አባ ዲዲሞስም ድንጋይ ነው ይላሉ አፍጥጠው። በቡጢም ይቃመሳሉ። ያን ሌሊት ፀጋዬ ሠቆቃው ጴጥሮስን ይፅፋል።ያን ሌሊት አባ ዲዲሞስም ጸጋዬ ቤት ዘው ብለው ገቡ።ያን ሌሊት 48ቱን ምስጢራዊ ቃላት በሰቆቃው ጴጥሮስ ውስጥ አርምባ ና ቆቦ በትኖ እንዲዘራቸው አዘዙት ወጣቱን ገጣሚ።ሚስጥሩን ጸጋዬ አያውቅም። ቢያውቅም አልነገረንም።ግን ዝም እንበል ብሎ ጽፏል። " አብረን ዝም እንበል" ብሏል።ሌላ ሚስጥር? ሌላ ቁልፍ? ከእንግዲህ "እሳት ወይ አበባ" የስነ-ግጥም መድበል መሆኑ አከተመ። የሚስጥራት ጎተራ እንጂ። እድሜ ለይስማዕከ!።

ለመሆኑ **"አክሳፎስ"** ምን ማለት ይሆን? በውስጡ ያዘለው ሚስጥርስ? እሳት ወይ አበባ ለህትመት ብርሃንና ሠላም ሲገባ አባ ዲዲሞስ አክሳፎስ የሚል የመጽሃፍ ረቂቅ ይዘው ገብተው ነበር። ሠቆቃው ጴጥሮስ በመድብሉ ውስጥ መካተቱንና በውስጡም 48ቱ ቃላት መኖራቸውን ለመሰለል። አክሳፎስ የሚል መጽሃፍ ግን እስካሁን አልታተመም። ዴርቶጋዳ እንጂ። ለከርሞ የምናነበውን ማን ያውቃል?

**አባ ዝንበሩ ራዕይ ናቸው!**
አባ ዝንበሩ ፤ አባ ፊንሐስ ፤ አባ ዲዲሞስ። ሦስት አባዎች። ሶስት ለነጻነት የተዋደቁ አርበኞች። በሚስጥራት የተሞሉ ካህናት።

"....ዋሻውን መቆፈር ስንጀምር(ሶስቱ አርበኞች)አላማችን ለራሳችን መደበቂያነት ለመጠቀም ነበር፡፡ በኋላም የሃገሪቱ ውድ ሃብቶችና የብራና መጽሃፍቶች ከጥፋት መከላከያ ሆኖ አገለገለ፡፡ እኔም በዚህ እየተቀየርኩ መጣሁ። ራዕዬን ከግለሰብ ራዕይነት ወደ ሃገር ራዕይነት አሸጋገርኩት..." አባ ዝንበሩ ናቸው ለዶ/ር ሚራዥ ይህን የሚሉት። አባ ዝንበሩ የዴርቶጋዳ ራዕይ ናቸው።ስለ መጪዋ ኢትዮጵያ፡- በብሩህ ራዕይ የተሞሉ አርበኛ።አባ ዝንበሩን ደግሞ የፈጠሯቸው፡- የጣና ገዳማት ጥንት ጥንታዊ የብራና መጽሃፍት ናቸው።ራዕይ ያስጨበጧቸው።

"ይህን ዋሻ ትልቅ ህቡዕ የምርምር ማዕከል አድርገው፤ መንግስታት ሲለዋወጡ የማይለዋወጥ፤ ለሃገሪቱ ህልውናና ሁለንተናው ልዕልና ጽኑ መሰረት የሚሆን ሚስጥራዊ ድርጅት የማድረግ ራዕይ በውስጤ ተጠነሰሰ።...ኢትዮጵያን ለኢትዮጵያዊያን ማድረግ የሚቻለው ትክክለኛው የቴክኖሎጂ ዕውቀትና ትክክለኛው የቴክኖሎጂ መሳሪያ በራሷ ልጆች እጅ ሲገባ መሆኑ ተረዳሁ። ይህን ራዕይ የተጋራኝ ሰው አለቃ አያሌው ብቻ ነበር። አያሌው ....... አባ ዲዲሞስ ይባል ነበር። ከአቡነ ጴጥሮስ ጋር ቅርርቦሽ ነበረው።...አቡነ ጴጥሮስ በባንዶች የጣሊያን አሽከሮች በጥይት ተደብድበው ሞቱ። ከዚህ ግዜ ጀምሮ ባህሪው(የአባ ዲዲሞስ) ተቀያየረብኝ።" ይህንንም አባ ዝንበሩ ናቸው ለዶ/ር ሚራዥ የሚያዋዩት።

**አባ ፊንሐስስ?**

አባ ፊንሐስ ስለ ሀገሩ ማሰብ አይፈልግም ።ኢትዮጵያ የሚለው ቃል ያንገሸግሸው ነበር፡፡...ሶስት አርበኞች፤ ሶስት አባዎች ፤ ሶስት መንገዶች። "ብሄራዊ-ራዕይ" ፤ "ስልጣን_ጥመኝነት"፤ "ፍቅረ-ንዋይ"።አባ ዠንበሩ ቀጠሉ፡- "በዚህ ዋሻ ውስጥ ብዙ ለውጦች ታይተዋል። ...ይህም የሆነው እንደ ኢንጅነር ሻጊዝ ያሉ ኢትዮጵያዊያን ሳይንቲስቶች በገንዘብም በእውቀትም አብረው መስራት ከጀመሩ በኋላ ነው።..." ሣይንቲስ እጅጉ ከአባ ዥንበሩ ጋር ? ባለ ራዕይው አርበኛ ከወጣቱ ሳይቲስት ? ተዓምር አያልቅም ! እንላለን በልባችን።...በአባ ዠንበሩ ንግግር ተደምመን፡፡

"ከኔ የሚጠበቀው ምንድነው ?" አለ ዶ/ር ሚራዥ ። "ሁለት ነገር ይጠበቅብሃል። አንዱ ቀሪ ህይወትህን በዚህ ድርጅት ውስጥ በማገልገል ሃገርህን ከጥፋት ማዳን ነው። በዚህ ሰአት ዓለም አቀፍ ማፍያዎች ከማይጠረቁት የመንግስት ባለ ሥልጣናት ጋር በመሻረክ ሃገርክን እየበዘበዝዋት ነው።" ለጥቂት ሰከንዶች አንገታቸውን ደፍተው ከተገዙ በኋላ ፡ "ማሔር ሻላል ሐሽ ባዝ" ብለው ቀና አሉ። "ምርኮ ፈጠነ ብዝበዛ ቸኮለ። ኢትዮጵያ ተስፋ በቀረጡ ወጣቶችና ሕዝቦች ተሞልታለች። የብዙ ኢትዮጵያዊያን መንፈስ ተሰብሯል።...ራሳችንን ለብዝበዛ ያጋለጥነው ራሳችን ነን፡፡ የጋራ ራዕይ ሊኖረን ይገባል።" አሉ አባ ዥንበሩ።

"ለዚህ ዓላማ ሌላው ከኔ የሚጠበቀው ምንድነው ?" አለ ዶ/ር ሚራዥ።

"የሰጠመውን መርከብ የምናወጣበትን ቁልፍ ስጠኝ"

"ምን?"

"በ 'ቶ' ቅርጽ የተሰራውን መስቀል መልስልኝ።"

"እሱ መስቀል ቁልፍ ነበር እንዴ?"

የዴርቶጋዳ ጉድ አያልቅም! እንላለን አሁንም በትረካው ሂደት ማዕበል እየተፈራገጥን። የሰጠመው መርከብ ምንድን ነው? ማንስ አሰተመው? ለምን? መስቀሉን ለሚራዥ ማን ሠጠው? የት አደረሰው? የዶ/ር ሚራዥና የአባ ዠንበሩ ግንኙነት መቼ ተጀመረ...?

**ሳይንቲስት ሻጊዝ እጅጉ ሕያው ነው**

ሳይንቲስት ኢንጅነር ዶ/ር ሻጊዝ ቅጣው እጅጉ፡- አሜሪካንን የህዋ ልዕለ ኃያል ካደረጓት አንዱ የሆነ፡ የኢትዮጵያዊ ልጅ ነው።ሳይቲስቱ ዕውቀቱን ፤ ንብረቱንና መላ እሱነቱን ለሃገሩ መስጠት ከጀመረ ጥቂት ዐመታት ተቆጥረዋል። ይህም የተለያዩ የዓለም መንግስታትን ከፍተኛ ጭንቀትና ሽብር ውስጥ ከቷቸዋል። ሳይቲስቱ ከአሜሪካን መዳፍ ውስጥ እንዳይወጣ ለ ሲ.አይ.ኤ ጥብቅ ትዕዛዝ ተላልፏል፡፡

የእሥራኤሉ **ሞሳድ** አፍኖ ለመውሰድ መረቡን ዘርግቷል።የራሽያው **ኬጂቢ** መሰናዶውን አጠናቋል።የኢትዮጵያ መንግስት የስለላ ድርጅቶችም የሳይቲስቱን ሕይወት የሚቀጥፉበትን አመቺ ግዜና ኣጋጣሚ እየጠበቁ ነው።

"ይህ ሰው እንኳንስ ጭንቅላቱና ሊቅነቱ ፤ አስከሬኑም ኢትዮጵያን አይረግጣትም" ሲሉ ዝተዋል፡፤ የኢትዮጵያ መንግስት የላካቸው ሰላይ ገዳዮች።

ሳይንቲስቱ በዓለማችን የሚገኙትን ራዳሮች፤ ሳታላይቶች፤ የመገናኛ አውታሮች በፈለገው ግዜ መዝጋት የሚችል አይምሮ ያለው ሠው ነው።...እናም ይህ ሰው ፊቱን ወደ ድሃ ሀገሩ መመለሱ ልዕለ ኃያሉን መንግስታት አስደንግጧል። ሳይንቲስት ኢንጅነር ሻጊዝ እጅጉ ተከቧል። በማንኛውም ሰዓት ህይወቱ ልትጠፋ ትችላለች።...በማንኛውም ሰዓት ከየትኛውም ስፍራ ታፍኖ ደብዛው ሊጠፋ ይችላል፡፤...ኢንጅነር ሻጊዝ ግን ራዕይ አለው....መንገደኛ ነው...ሩቅ አላሚ...ሩቅ ተጓዥ.....።

“ኢትዮጵያ መጪው ተከታታይ ትውልድ ከፍሎ የማይጨርሰው ብድር ተበድራለች።እያንዳንዱ ወጣት እያንዳዱ ታዳጊ የሚወርሰው ሌላ ነገር የለም።...የገንዘብ ዕዳ....፤ የሞራል ዕዳ..፤ የደም ዕዳ...፤!!። ኢትዮጵያዊያን ዩራኒየማቸው ላይ ቆመው እየለመኑ ነው።....ነዳጃቸው ላይ ቆመው፤ ነዳጅ አጥሯቸዋል..!። ኢትዮጵያዊያን ጥቁር አልማዛቸው ላይ ቆመው እየተመጻወቱ ነው።...ወንድሜ ሚራዥ...እኔና አንተ እስከመቼ ዝም እንላለን?....ስለዚህ ጉዳይ እስከመቼ ዳር እንቆማለን?” የሳይንቲስቱ ንግግር እንደ ሠደድ እሳት ሲለበልበን ይሰማናል። እከ መቼ?.....

“እስከ መቼ? አለ ሚራዥ ውስጡ ተቃጥሎ” እኔ በበኩሌ ከአሁኗ ደቂቃ ጀምሮ ማንኛውንም ተግባር ለመፈጸም ዝግጁ ነኝ! ግን ምን ማድረግ እችላለሁ? የችግሩ ሰንሰለት ተቆርጦ የማያልቅ ነው። የሰው ኃይልና በቂ ገንዘብ ያስፈልጋል።” ይላል ሚራዥ። እኛም ሚራዥን ተከትለን፤ ዕውነት ነው! ምን ማድረግ እንችላለን ? እንላለን! የሚራዥን ጥያቄ በደመ ነፍስ እንደግማለን።እናስተጋባለን።

ሳይቲስቱ ደግሞ ዕውነት አይደለም ይለናል። “ የሚያስፈልገው በቂ ገንዘብ ብቻ አይደለም፤ የሚፈለገው ብዙ ሕዝብም አይደለም። ልብ ለልብ ተገናኝተን አብረን ከሠራን እንኳንስ አንዲት ሃገር ዓለምን መለወጥ የሚችል ዕውቀት አለን” ይለናል! ዕቅጩን ይነግረናል፤ በውስጣችን የጠወለገችውን ተስፋ ያለመልማታል፡፡ ሳይንቲስት እጅጉ።
“ይልቅ እኔም አንተም ሞት ሳይቀድመን ወገኖቻችንን ከሞት የምንታደግበት ወቅት ላይ መሆናችንን አስብ፡፡ ኢትዮጵያዊያን አንገታቸውን የደፉበት ወቅት ላይ ነን። ኢትዮጵያም ተስፋ በቆረጡ ወጣቶች ተሞልታለች።ራዕይ ያጡ ሕዝቦች ኀተራ ሆናለች።ራዕይ የሌለው ሕዝብ ደግሞ ይጠፋል።የተስፋው መስኮት መከፈት አለበት!፡፡ ኢትዮጵያን ሌላ ሰው መጥቶ አይለውጥልንም።ኢትዮጵያ ውስጥ ሽር..ብትን የሚሉት ቻይናዎችና ኢንዲያንስ ሁሉ ፡- ላንተ ብልጽግና ግድ የላቸውም። ሃገርክን ከቅጥረኞችና ከወሮበሎች የምታድነበት ግዜ አሁን ነው።”ስይቲስቱ ለሚራዥ ።

“አንድ ጥያቄ እንድጠይቅ ፍቀድልኝ”ሚራዥ ነበር
“ጠይቀኝ”
“ወደ ጦር ሜዳ እየላከኝ ነው?”
ሻጊዝ ከት ብሎ ሣቀ፡

እንሆ! በጀንዋሪ 13-2006 ከአሜሪካ ቴክሳስ ታላቅ የሃዘን ዜና በዓለማችን ህዋ ላይ ኖኘ።የሳይንቲስት ኢንጅነር ዶ/ር ሻጊዝ እጅጉ ዕልፈተ-ሕይወት።

ወደ ድሃ ሃገሩ ፊቱን በመመለስ እሱነቱን አሳልፎ በሠጠ፤ ሃገሩንም ከግፈኞች ለመታደግ የፖለቲካ መዋቅር በዘረጋ በሁለት ዓመት ውስጥ ኢትዮጵያዊው የህዋ ሳይቲስት ሻጊዝ እጅጉ በተወለደ በ58 ዓመቱ ከዚህ ዓለም በሞት ተለይቷል አሉን አሜሪካኖች።ዕውነት ነው አሉ።ህይወቱን ሊቀጥፉ የነበሩት ቅጥረኞቹ የኛው ጉዶችም ከቀጣሪዎቻቸው ጋር በደስታ ሰክረው ውስኪ እያደቀደቁ፤ ከበሮ እየደለቁ ጮቤ ረገጡ። አዎ! ሳይቲስ እጅጉ ሞት ሳይቀድመን፡-ብሎ ተንብዮ ነበር፡፤ ግና ሞት ቀደመው፡፡ ዕውን ሳይቲስት እጅጉ የሞተው ተፈጥሯዊ ሞት ነውን?

---

**ሳይንቲስት እጅጉ አልሞተም**

በዴርቶጋዳ ፤ በ-ዴር33 ፤ በዳጋ እስጢፋኖስ ከርሰ ምድር - በሃገሩ -ዘላለማዊ ሕይወትን ተቀዳጅቷል።ሻጊዝ እጅጉ በሕይወት የለም። አርማው ግን አልወደቀም። በዶ/ር ሚራዥ በሲ.አይ.ኤዋ **ሜሮድ**፤ በሞሳዷ **ሲጾራ**፤ በአሜሪካ አየር ኃይል ዝነኛ ፓይለት በነበረው **ጌራ**፤ በቁጥር 2 ዴርቶጋዳ ሳይቲስቶችንና ምሁራን በዴር 33 ራዕይ ዛሬም የሳይቲስቱ ዓርማ አለ። ሳይንቲስት እጅጉ አልሞተም።በድፍን ኢትዮጵያ ልጆች ልብ ውስጥ ዛሬም ህያው ነው፡፡

**ዶር 33፡-** በሳይንቲስት እጅጉ የተነደፈች ፤ በዴርቶጋዳ ምሁራን ሕልውና ያገኘች፤ እንደ መኪና በየብስ፤ እንደ ዶልፊን በባህር፤ እንደ አሞራ በሰማይ፤ የምትበር፡-የተራቀቀች የዴርቶጋዳ ውጤት ነች፡፡ ዴሬ 33 የዴርቶጋዳ ምሁራን ራዕይ ተምሳሌ ናት። ዶር 33 የሳይንስ ልቦለድ ናት አትበሉ።

ሳይቲስት ሻጊዝ እጅጉ ህዋን ድል ያደረገ መንኮራኩር አልነደፈምን?ዛሬ ዓለም የሚገለገልበት፤ አቅጣጫ አመልካች(ጂ.ፒ.ኤስ) አልፈለሰፈምን? ታዲያ ዶር 33 እንደምን የሳይንስ ልቦለድ ልትሆን ትችላለች። ዶር 33 ራዕይ ናት። የአባ ዡንበሩ ራዕይ። የሻጊዝ ራዕይ። የወጣቱ ትውልድ ራዕይ።

ይልቅ ለዚህች ልዩ የወጣቱ ትውልድ ራዕይ፤ 33 ቁጥር ለምን መታወቂያዋ ሆነ? ብለን እንጠይቅ፡- አዎ እየሱስ ክርስቶስ የሰውን ልጅ ከዘመናት ባርነት ሊያወጣ፤ ከሃጢያቱም ሊያጸዳው፤ራሱን አሳልፎ በመስቀል ተቸንክሮ የሞተው በ 33 ዓመቱ አልነበረምን? የዴር 33 ተምሳሌነትስ ምን ይሆን? ይህ ወጣት ትውልድ-የሃገሩ መድህን፤ የሃገሩ ፤ ትንሣኤ አጋፋሪ፤ የሃገሩ ራዕይ ፤ .....ሆኖ ሃገሩን ከምትገኝበት መከራና ችግር ይታደጋት ዘንድ፤ ወገኖቹንም ከግፍ አገዛዝ ነጻ ያወጣ ዘንድ....አመላካች ትሆን?

**ወጣቱ ትውልድ በአባቶቹ ሐጢያት አይኖርም**

**አባ ፊንሐስ** ወንጀለኛ ናቸው። አባ ፊንሐስ የሃገር ቅርስ ሰርቀው የሸጡ ናቸው። አባ ፊንሐስ ከሃገራቸው ብሶትና ሰቆቃ ይልቅ ግላዊ ሕይወታቸው የሚደላደልበትን ህልም ሲያልሙ፤ ለዚህም ዕውን መሆን ደፋ ቀና ሲሉ የኖሩ ናቸው፡፤ አባ ፊንሐስ ስለሃገራቸው ምንም መስማት አይፈልጉም።ስለ ነዋይ ብቻ እንጂ።አባ ፊንሐስ የንዋይ ፍቅር ያነሆለላቸው አባቶች ተምሳሌ ናቸው፡፤ በየትውልዱ ብዙ ፊንሐሶች ተፈጥረዋል። ዛሬም አሉ።

**ሲጳራ፡-** የአባ ፊንሐስ ልጅ ናት። ሲጳራ በአባቷ ወንጀል አልኖረችም።የሞሳዲ ሲጳራ በአባ ዡንበሩ ራዕይ ተጠመቀች። በሚራዥ ፍቅር ተንበረከከች።በዴርቶጋዳ ለትንሳኤ ኢትዮጵያ ቆመች።ሲጳራ የዚህ ትውልድ፡- የወጣቱ ትውልድ፡- ተምሣሌ ናት።

አርበኛው አባ ዲዲሞስ ረቂቅ ናቸው፡፤ አባ ዲዲሞስ አዋቂ ናቸው፡፡የተማሩ፡፡አባ ዲዲሞስ ራዕያቸውን የሥልጣን ጥማት አባዜ ያኮላሸባቸው ናቸው።የአባ ዲዲሞስ ዕውቀትና ራዕይ ሥልጣን ነበር። በአቡነ ጴጥሮስ ላይ ያሰሙትም ሮሮ “ሥልጣን ሳትሰጠኝ ፡ አቡነ ዲዲሞስ ሳታስብለኝ” ለምን ሞትክ? በማለት ነበር። ከአባ ዡንበሩ መገንጠላቸው ሚስጥሩ የሥልጣን ጥማቸው ነበር፡፡ አባ ዲዲሞስ በየትውልዱ ዕውቀታቸውንና ጥበባቸውን ለድብቅ የስልጣን ጥማቸው ማርኪያ አውለው ያኮላሹ አባቶች ተምሳሌ ናቸው። እንዲህ ያሉ የአዋቂ አጥፊዎች በየትውልዱ ተፈጥረዋል። ዛሬም በገፍ አሉ።

**አባ ዡንበሩ፡-** አርበኛ ናቸው። ታሪክ፤ነጻነት፤ቅርስና ባህላችንን ጠብቀው ለትውልድ ያስተላለፉ ክቡራን አባቶች ተምሳሌ ናቸው። ለኢትዮጵያ ክብር፤ ልዕልና እና ብልፅግና ራዕይ የነበራቸው አባቶቻችን ተምሳሌ ናቸው። አባ ዡንበሩ ሞቱ! ራዕያቸው ግን አልሞተም። የአባ ዡንበሩ ራዕይ በሳይንቲስት ሻጊዝ ዕጅጉ ውስጥ ዕውን ሆነ፡ኖረ። ሻጊዝም የአባቶችን አደራ ተረካቢ ትውልድ ተምሳሌ መሆኑ ነው።ሳይንቲስት እጅጉ ሞተ። አርማው ግን አልወደቀም ። ዶ/ር ሚራዥ በአባ ዡንበሩ ቡራኬ ተሰጥቶታል። ራዕያቸውን ዴርቶጋዳን ተረክቧል። የሳይንቲስት ሻጊዝን አርማ አንስቷል። ዶ/ር ሚራዥ የዚህ ትውልድ ተምሳሌ ነው።ትንሳዔን የሚያመጣው ትውልድ። ዛሬ የምናየው ይህ ትንታግ ወጣት ትውልድ !።

ወታደር-ዶ/ር ዥንጊዳ ሞተ። በዳጋ እስጢፋኖስ ከርሰ-ምድር ተቃጠለ። የዥንጊዳ ራዕይ ግን አልተቃጠለም። በሲ.አይ.ኤዋ ሜሮዳ ፤ በሞሳዲ ሲጳራ ፤ በአሜሪካ አየር ኃይል ዝነኛ አብራሪ በነበረው ጌራ(የዴር 33

ካፒቴን/ሹፌር/ፓይለት) ውስጥ አለ።እነኚህ የዚህ ወጣት ትውልድ ተምሳሌ ናቸው።በአባቶቻችን መልካም ራዕይ ውስጥም ይኖራሉ። በአባቶቻችን ግፍ ፤ ወንጀልንና ምዝበራ ውስጥ ግን አይኖሩም።"በዴርቶጋዳ ራዕይ ውስጥ እንጂ። ኢትዮጵያን የሚታደጋትም ይህ ወጣት ትውልድ ነው። ነጻ የሚያወጣትም ይህ ትውልድ ነው። ይህ ወጣት ትውልድ ክንዱን አጠንክሮ ይነሳል። ባንዲራዋን ከፍ አድርጎ ያውለበልባል። ይዘምራልም።.....ይተማልም.....!

***<u>መሸበቢያ</u>***

ዴርቶጋዳ፡-በሤራ የረቀቀ ፤በቋንቋ የመጠቀ፤ በገጸ-ባህሪያት ሕያው የሆነ፤ በምናብ ህዋን የጠለቀ፤ተስፋና ራዕይ ያነገበ፤ ዛሬና ትናትን፤ ዛሬና ነገን ያቆራኘ፤ የዚህ ወጣት ትውልድ የፈጠራ ውጤት ነው። የይስማዕከ ወርቁ ገፀ-በረከት።

ክብር የእግዚአብሔር ነው።ምስጋናም በእግዚአብሔር ስም ዴርቶጋዳን ላስነበበከኝ፡- ለብላቴናው ይስማዕከ ወርቁ፡- ክብር ምሥጋናዬ በላይኛው ፈጣሪ ሥም ባለህበት ይድረስህ።

የላይኛው ፈጣሪ መልዕክተኛ በውድቅት ሌሊት በድቅድቅ ቾለማ ከተኛህበት ደግሞ ደጋግሞ ይቀስቅስህ።ከራስጌህም ቆሞ መለኮታዊ ብርሃን ያብራልህ። ከክንፋም ላባ ነቅሎ፤እንደ ብዕርም ቀርጾ በእጅህ ያስጨብጥህ! መለኮታዊ መልዕክቱም በመለኮታዊ ልሣን ይገለጥልህ!። ያንንም በብራና ትከትበው ዘንድ፤ ተስፋ ላጣው ለተስፋይቱ ምድር ታደርስ ዘንድ ብርታቱንና ፅናቱን፡ ይስጥህ!። ዛሬም ነገም ለዘላለሙ አሜን!።

**እንባቢ ሆይ!** እንሆ ጨረስኩ! ተነፈስኩ! እኔም ወጥሮ ከያዘኝ ጭንቀት ተገላገልኩ፤ እናንተም እኔን ተገላገላችሁ። አዎ! ስለ ይስማዕከ ወርቁ፡- "ዴርቶጋዳ" አንባቢን በቂ ግንዛቤ አስጨብጫለሁ ብዬ አልገበዝም። ምክንያቱም ጥልቅና ረቂቅ ስለሆነው ዴርቶጋዳ እኔም በቂ ግንዛቤ መያዜን እርግጠኛ አይደለሁምና ነው።ብቻ ግን አንድ እርግጠኛ ሆኜ የምነግራችሁ ነገር አለ፡- ዴርቶጋዳን የግድ ማንበብ እንዳለባችሁ፤ እንደ ሚገባችሁ እነግራችኋለሁ። ይኸው ነው!

በያለንበት ቸር ይግጠመን
መስፍን ማሞ ተሰማ
ሲድኒ አውስትራሊያ
ሰኔ መባቻ 2002